ማንኛውም ሰው የጡት የማህጸንና የኣንጀት ነቀርሳ (ካንሰር) ተጠቂ ሊሆን ከፍተኛ ችሎታ ስላለው ይህን ለመቆጣጠር በግዜ ተገቢው ህክምና ለማግኘት በተዘጋጁት የህክምና ኣጋጣሚዎች መሰተፍ ይገባል።

እስካሁን በዚህ ኣጋጣሚ ያልተሳተፉት ወይም እድሜ ያልቀረባላቸው ከታች በተጻፈው ስልክ ቁጥር በመደወል ቀተሮ መያዝ ይችላላኡ።

- ክፍያ የሌለው የነጻ ቁጥር 800 536 693
- ኢሜል በመላክ uocpomas@aslroma1.it
- በኦንላይን ቀጠሮ በመያዝ hiips://prenotascreening.regione.lazio.it ገብታቹ Prenota Smart ላይ ማስቀጠር

እነዚህ ምርመራዎች ከክፍያ ነጻ ሆነው ከሃኪማቹ የትእዛዝ ወረቀጥ ኣያፈልጋቸውም።

ልክ ምርመራውን ኣድርገው እንደጨረሱ ውጤቱን ለማወቅ ስልክ ቁጥራቹና ኢሜላቹ እንድትሰጡ ይጠየቃችዋል

ሂወት ማዳን በሚችሉት

የህምና ኣጋጣሚዎች

መሰተፍ ይገባል

MINISTERO DELL'INTERNO

# በግዜ ጤናቹ መንከባከብ መሰላቹ ነው



REGIONE TOSCANA

Regione Emilia-Romagna

REGIONE LAZIO

REGIONE SICILIANA

### ነጻ የጡት ምርማራ

የጡት ነቀርሳ ወይም ካንሰር በከፍተኛ ደረጃ ሴቶች የምያጠቃ ነቅርሳ ነው።

### የምርመራው ኣደራረግ ዘዴ

በመጀመርያ የጡት ኤክስረይ ይደረጋል፣ ቀጥሎ ኣስፈገላጊነት ካለው ተጨማሪ ምርመራዎች ይደራጋሉ።

የምርመራው ውጤት ነጻ ከሆነ መልስ በደብዳቤ ይላካል። መልስ ካልመጣ እላይ በተጻፈው ስልክ ቁጥር በመደወል ወይም ኢሜል በመጻፍ ውጤቱን ማግኘት ይቻላል።

### የምርመራው ተጠቃሚዎች

ይህን ምርመራ ከ25 እስከ 64 ዕድሜ ላላቸው ሴቶች ይመለከታል

### በየስንት ግዜ

እድምያቸው ከ 25 እስከ 29 የሆኑትን ሴቶች በሶስት ኣመት ኣንዴ ከ 30 እስከ 64 የሆኑትን ደግሞ በኣምስት ኣመት ኣንዴ እንድያደርጉት ይመከራል

### ነጻ የኣንጀት ምርመራ

የኣንጀት ነቀርሳ (ካንሰር) ሴቶችና ወንዶች በብዛት ያጠቃል። የኣንጀት ነቀርሳ ምልክቶች ከሆኑት ኣንድ በኣይን የማይታይ ሰገራ ውስጥ ደም ሲኖር ነው።

### የምርመራ ኣደራረግ ዘዴ

የሰገራ ምርመራ ከተደረገ በሃላ ደም እንዳለ ከተረጋገጠ ተጨማሪ ምርመራዎች እንዲደረጉ ይጠየቃል ። ለማንኛውም ሰገራ ውስጥ ደም መኖር ማለት በቀጥታ ነቀርሳ መታመም ማለት ኣይደለም። ሆኖም ግን ከነቀርሳ ግኑኝነት እንደሌለው ለማረጋገጥ ተጨማሪ ምርመራዎች ማድረግ ያስፈልጋል።

የምርመራው ውጤት ነጻ ከሆነ መልስ በደብዳቤ ይላካል። መልስ ካልመጣ  እላይ በተጻፈው ስልክ ቁጥር በመደወል ወይም ኢሜል በመጻፍ ውጤቱን ማግኘት ይቻላል።

### የምርመራው ተጠቃሚዎች

ይህን ምርመራ ከ50 እስከ 74 ዕድሜ ላላቸው ሴቶችና ወንዶች ይመለከታል

### በየስንት ግዜ

ይህን ዓይነት ምርመራ በየሁለት ኣመት ማድረግ ይገባል

.

### ነጻ የማህጸን ምርመራ

የማህጸን ነቀርሳ ወይም ካንሰር (የላይኛው የማህጸን ክፍል) በግዜ ተለይቶ ተገቢው ህክምና ካላገኘ ኣደገኛ ሊሆን ይችላል።

### የምርመራው ኣደራረግ ዘዴ

ፓፕ ተስት (Pap test) እና HPV የሚባለው ምርመራ ከላይኛው የማህጸን ክፍል ህዋሳት በመውሰደና በመመርመር የሚደርግ የምርመራ ዘዴ ነው። ለሴትዋ ምንም ኣደጋ ወይም ህመም የማያስከትል ምርመራ መሆኑን ማወቅ ያስፈልጋል። የዚህ ምርመራ ውጤት ልክ እንደተገኘ ኣስፈላጊነት ካለው ተጨማሪ ምርመራ ይጠየቃል ውጤቱ ነጻ ከሆነ መልስ በደብዳቤ ይላካል። መልስ ካልመጣ እላይ በተጻፈው ስልክ ቁጥር በመደወል ወይም ኢሜል በመጻፍ ውጤቱን ማግኘት ይቻላል።

**የምርመራው ተጠቃሚዎች** ይህን ኣይነት ምርመራ እድምያቸው ከ25 እስከ 64 ለሆኑት ሴቶች ይመለከታል።

**በየስንት ግዜ** እድምያቸው ከ25 እስከ 29 ለሆኑት ይህን ምርመራ በየሶስት ኣመት ኣንዴ ሆኖ እድምያቸው ከ30 እስከ 64 ለሆኑት ደግሞ በኣምስት ኣመት ኣንዴ እንድያደርጉት ይመከራል።